# ዋ!...አሲምባ...

ዋ!.. አሲምባ......

የትግል አምባ
የፍቅር አበባ
የሕይወት አምባ
ዝምታህ አስተጋባ
ታሪክህ ይዘገባ
እኮ ቃልህ ወዴት ገባ?

ዋ! አሲምባ...

የትግል መሰረት
የኢሕአፓ ጽናት
ለኢሕአሠ ኩራት
የጀግና ብሥራት
ቤተ ሰማዕታት።

ዋ! አሲምባ...

አሲምባ... የደም መሬት
የጀግና ቤት
ከእቅፍህ የወደቁት
ለነፃነት የተሰውት
አርአያቸው ይሁን ሕይወት
አታውርሰን እኮ ትዝብት።
አሲምባ ለፋሺስት ውጋት
ለወያኔ የውስጥ እሳት
ለሻዕቢያ የግር እሳት
ለፊውዳል የሞት ብስራት
እኮ ዛሬ ወዴት ወዴት?

ዋ! አሲምባ...

አሲምባ ጀግና ተወልዶበት
ጀግና ያደገበት
ጀግና የቀረበት
አሲምባ የትግል ቤት
እኮ ዛሬ ወዴት ወዴት?

ዋ! አሲምባ...

አሲምባ እስቲ አግሳ
ድምጽህ ይድረስ ዛል አንበሳ
ከበሮው ይመታ
ይነፋ እምቢልታ
ይሰብሰብ ያ ጋንታ
ሆኖ መንታ መንታ።

ዋ! አሲምባ...

ይንጫጩ ወፎቹ
ድምፅ ያውጡ ዛፎቹ
ይሰማ ዜማቸው
ይድመቅ ፉጨታቸው
ፍጥረታት ያጓሩ
እንደየቃናቸው ሁሉም ይዘምሩ።
ፀጥታው ይገሰስ
አየሩ ይንቀሳቀስ
አራዊት ይደንሱ
ወንዞችም ይፍሰሱ።
ማዕበሉ ይናወጥ
ፍጥረት አይቀመጥ
ይፍለቅብት ሕይወት
ባሩድ ይሸተትበት
ምሱ ይቅረብለት
ለዚያ የጀግና ቤት
አለመደምና እባዶ ቤት ኩራት
አደራውን መብላት
የሀገርን ነፃነት።

ዋ! አሲምባ...

ተነሱ ዘምሩ
ጥራኝ በሉ ዱሩ
ፋኖ ተሰማራ
በጃናሞራ
ባሲምባ ተራራ
ይታደስ ሕይወቱ ይንቃ ከእንቅልፉ
አይቀሬ ነውና ትግል ማንዘፍዘፉ።

ዋ! አሲምባ...

ናፈቀኝ አፈሩ
ቆንጥር ሥራ ሥሩ

ጋራ ሸንተረሩ
አሲምባ ደብሩ።
እንቅፋቱም ይምታኝ
ገደሉም ይሳበኝ
ቆንጥርና ሾሁ ይውጋና ያቁስለኝ
የነፃነት ቤቴ ዳግመኛ ናፈቀኝ
አሲምባ ጋሻዬ ዳግም ተቀበለኝ
ቤት ለምቦሳ በለኝ።

ዋ! አሲምባ...

ትንሳሄያቸው ይሁን ለኛ ለወጣቶች
በጉያህ ላሉቱ
ሕይወቴ አሲምባ ብለው ለቀሩቱ።
ይስጠን ጥንካሬ
አፅማቸው ለዛሬ
ዘብ ልቁም ለሀገሬ
ይወልወል ዝናሬ።
ይጥራኝ መንፈሳቸው
ትግል ሕይወታቸው
አጥንታቸው ይውጋኝ
ጋሬጣ ያልብሰኝ
ቃል ኪዳን በልቼ
እርማውን ከድቼ
ፅናቴን አጥቼ
በቁሜ ከሞትኩኝ።

ዋ! አሲምባ...

አሲምባ የደም መሬት
አሲምባ የቁም እሳት
ሆነህ ትቀር የጀግና ሐውልት?
ጮራ ነበርክ ለነፃነት
የኩሩ ትውልድ ተምሳሌት
የኢሕአፓ ሐሴት
የህዝብ ስሜት
እኮ አሁን ወዴት ወዴት?

ዋ! አሲምባ...

የጣር ጩኸት ሲያስተጋባ
ፍሬ ሲለይ ከገለባ
ከእቅፍህ ያረካቸው
በእንቀልባህ ያዘልካቸው

ይጠራኛል ልሳናቸው
የደም ገንቦ ኩራታቸው
ይታየኛል ያ አርማቸው
የነፃነት ተምሳሌያቸው
ለዘመናት መዝሙራቸው
የኩሩ ትውልድ አርአያቸው
ኢትዮጵያዊነት መለያቸው
ኢሕአሠ መሎያቸው
የዓላማ ጽናታቸው።

ዋ! አሲምባ…

ቆጠቆጠኝ፤ ቀነቀነኝ
የቁም እንቅልፍ እያስተኛኝ
መራር ፅዋ እየጋተኝ
እምቢልታውን ሲነፋብኝ
ብረት አንሳ ተከተለኝ
ፋኖ ሁነህ ፋኖ አድርገኝ
አሲምባዬ ዳግም ጥራኝ…
………………………ዳግም ጥራኝ።
ዋ!……አሲምባ………..

ከአሉላ